"ዳንኤል ተጫኔ" በሚል ስም፡ የአንድ የመነኵሴ መልክ ብርሃናዊ ሥዕል፡ ከጎኑ ከተለጠፈበት ሰው፡ "አሳዛኝ ቃል!" በሚል ርእስ፡ በፌስቡክ መድረካችን ላይ ለተጻፈልኝ የይድረስ ደብዳቤ፡

እኔ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ አጭር መልስ አቀርባለሁ።

በቅድሚያ ግን፡ በዚህ ስምና ብርሃናዊ የሥዕል መልክ፡ በትክክለኛ ማንነታቸው፡ አባ ወልደ አረጋዊ ወልደ ሥላሴ የተባሉት ሰው፡ በዚሁ በፌስ ቡክ የጎዋ መድረካችን ላይ፡ በየጊዜያቱ፡ ደጋግመውና አከታትለው ካሠፈሯቸው በርካታ ጽሑፎች መካከል፡ አንዱን ብቻ፥ እኔም ከሰጠኋቸው አስተያየቶች መካከል፡ አንዱን ብቻ፡ ለትዝብትና ለዓይነት ያህል፡ እዚህ ላይ ጠቅሻቸዋለሁ።

<u>ከበርካታዎቹ መካከል፡ አንዱ፡ የእርሳቸው ጽሑፍ።</u>

*የእውነት ልጅ ንቡረ እድ ኤርምያስ! ከልብ እናድዎታለን፤ እባክዎ ለዚህ ክፉ ትውልድ ቁርጥ ፍርድዎትን ያስተላልፉ! ሁሉ ይወቀው! የኢትዮጵያ ስውራን፡ ስለርስዎ አብዝተው ሲጮሁ አየሁ። ምንኛ የታደሉ አባት ነዎት!? እርሱ ይፍቀድና አይንዎትን ያሳየኝ! አባታችን እንቁ ነዎት! ግን ያወቀዎት የለም። እናዝናለን።*

\+ + +

<u>ከበርካታዎቹ መካከል፡ ለዚህ ጽሑፍ፡ ከእኔ የተሰጠ፡ አንዱ አስተያየት።</u>

እርስዎ፡ የተገለጸልዎትንና የተረዱትን፥ የሰሙትንና ያዩትንም እየተናገሩና እየጻፉ ስለኾነ፡ ኹሉን የሚያውቅና የፍርድ ባለቤት የኾነው መንፈስ ቅዱስ፡ የዚህ ተልእኮዎን ዋጋ፡ እርሱ ባወቀና በፈቀደ ይከፍልዎታል። በእኛ በኩል ግን፡ ስለአሳብዎና ስለአሳቢነትዎ፥ ስለማሳሰቢያዎና ስለመልካም ቃሎችዎ፡ "እግዚአብሔር ይስጥዎ!" እንልዎታለን።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷም፡ በአምላክ እናት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም እና በተወዳጁ ልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት ተመሥርታና ጸንታ፥ በአዳምና ሔዋንም ጥንተ ተፈጥሮ፡ ተከሥታና በገሃድ ተገልጻ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምራ እስከዛሬ፥ ዛሬም፡ እነሆ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ዘንድ፡ በሰማይም፥ በምድርም፡ እውን ኾና እየሠራች ትገኛለች። ወደፊትም፡ በዚሁ መለኮታዊና ዘለዓለማዊ ህልውናዋ ትቀጥላለች።

ይህ እውነታ፡ በዚህ: በፌስቡክና በዋናው የጎዋ ሰሌዳዎቻችን ላይ፡ በቅርቡ በወጣው ቃለ ዐዋዲ (የነጋሪት ቃል)፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ ታውጇል። ስለዚህ፡ በመለኮት እንደበት፡ "**ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዓ፡ ለይስማዕ!**"፡ ማለትም፡ "**የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!**" የሚለውን ምክርና ማሳሰቢያ፥ ማስጠቀቂያና መፋረጃ፡ በመደጋገም ይኸው፡ በአዋጅ ከማስሰማት በቀር፡ በእኛ በኩል፡ ሌላ የምንለውና የምናደርገው፡ የቀረ ተግባር የለም።

ቢኖርም፡ አንድ ነገር ብቻ ነው። ያም፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል፡ እንደገና ተደግሞ ሊገለጽ ይቻላል፡-

የእግዚአብሔር መንግሥትና እናት አገራችን ኢትዮጵያ የኾነችው፡ የአምላክ እናት ድንግል ማርያም፥ "**ወትቤሎሙ እሙ፡ ለእለ ይትለአኩ፡ 'ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!'** ብላ፡ ለቃና ዘገሊላ፡ የሠርግ አገልጋዮቻቸው እንደተናገረች፡ አኹንም፡ በእውነትና በታማኝነት፡ ልጆቿ ለኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "**ልጄ፡ የሚላችሁን ኹሉ፡ ስሙት! አድርጉትም!**" ብላ፡ በዚያ፡ የቃለ ዐዋዲ መልእክቷ፡ በእናትነቷ የሰጠቻቸውን መመሪያ የተቀበሉ ከኾነ፥ ሰው የኾነው ልጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሊያደርጉት ስለሚገባቸው የኢትዮጵያዊነት ምግባር፡ በዚያ፡ የአዋጅ ቃሉ የነገራቸውን ሰምተው፡ በተግባር ላይ ማዋልና ለፍሬ ማብቃት ብቻ ነው።

ይህን የኢትዮጵያዊነት ግዳጃቸውን፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው ፈጽመው በሚገኙበት ጊዜ፡ የሚደርሰው ተአምራዊ ትንግርት፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ በፊታቸው ገዝፎ ያዩታል። ያም፡ ባለማመናቸው ምክንያት የተሠወረችባቸው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በገሃድ ትከሠትላቸዋለች፤ በሰውነታቸውም ውስጥ፡ እንደእስትንፋሳቸው ትመላለች፤ እንደፀሓይዋ ብርሃን ይጎናጸፏታል፤ እንደውኃው ይጠጧታል፤ እንደምድሪቱም ይቆሙባታል፤ እርሷንና እየራሳቸውን፡ እንዲህ፡ እውን ኾነው ያገኟቸዋል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ በዚያን ጊዜ፡ አምላካቸውና አባታቸው፥ ሊቀ ካህናታቸውና አጼያቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እንደዚሁም፡ አገራቸውና እናታቸው፥ ሃይማኖታቸውና ንግሥታቸው፡ ድንግል ማርያም፡ በየዙፋናቸው ተቀምጠው፡ እያንዳንዳቸውን፡ በታላቅ ደስታ ሲቀበሏቸው፡ እየራሳቸውን ያገኛሉ።

ይህ ተአምራዊ ትንግርት፡ የእነርሱ፡ የእያንዳንዳቸው "ትንሣኤ" ይኾናል። በቅዱሱ ኪዳን ላይ በፈጸሙት፡ ግልጽ ክህደትና ዓመፅ፥ ክፋትና ኃጢአት ምክንያት፡ እየራሳቸውን፡ ሙታን አድርገው፡ ለሙታኑ ዓለም ስለዳረጉ፡ እውነተኞቹንና ታማኞቹን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቿን ዐቅፋ፡ በዘለዓለማዊው የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት፡ ህልውናዋን ቀጥላ የምትገኘው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ ተሠውራባቸው የነበሩት፡ እነርሱ፡ በቀዳሚው የመንፈስ ትንሣኤ ለመነሣት በመብቃታቸው፡ አዎን! ያ ጊዜ፡ የእነርሱ ትንሣኤ ይኾናል። በፈጣሪያችን ዘንድ፡ "የኢትዮጵያ ቀን!" ተብሎም፡ መልካሙ ምሥራች ሲነገርበት ይኖራል።

\+ \+ \+

ታዲያ! ይኼ፡ የአኹኑ ጽሑፍዎ፡ እውነተኛ ምንነትዎንና ማንነትዎን፥ ተልእኮዎም ምን እንደኾነ፡ ያጋለጠ ከመኾኑ ጋር፡ ራስዎን፡ "በአንድ ራስ፡ ኹለት መላስ!" ያሰኘዎ አልኾነምን? አዎን! በእርግጥ አሰኘዎ እንጂ።

ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይድረሰውና፡ ለነገሩ፡ እኔም፡ ቀደም ብዬ፡ ማንነትዎንና ተልእኮዎን፥ አመጣጥዎንና አቀራረብዎን ስላወቅሁት፡ የወረወሩትን፡ የከንቱ ውዳሴ ፆር፡ እንዴት አድርጌ፡ ወደራስዎ እንደመለስሁት፥ መሠሪ መልእክትዎንም፡ በመንፈስ ቅዱስ እውነት፡ እንዴት አቃንቼ፡ ወደአንባቢዎቻችን እንዳስተላለፍሁት፡ ከላይ ከተጠቀሰው፡ ከራሱ፡ ከሰጠሁዎት፡ የመልስ ጽሑፌ፡ ማንም አስተዋይ ተመልካች፡ በቀላሉ መረዳትና መገንዘብ ይቻለዋል።

ከዚህ ቀጥዬ፡ በአኹኑ የነቀፋ ጽሑፍዎ፡ ላቀረቡት ጥያቄና ለሠነዘሯቸው ኃይለ ቃላት፡ ተገቢውን መልስ እሰጣለሁ፡-

፩ኛ፡ *"ንጉሥ ቴዎድሮስ ዘኢትዮ... የሚለው ጽሁፍ፡ ለእርስዎ ተጽፎ የደረሰዎት ከመልእክቱ እንዳየሁት ህዳር 14 1995 እስከዛሬ መልስ ሳይሰጡበት ቀርተው ነው ወይስ ፊት የሰጡት መልስ ነው? ከሆነስ አሁን እንደገና ይህን ሀሳብ ለምን ማንሳት ፈለጉ? አላማው ምንድነው?"* ላሉት፡ መልሱ፡ ባጭሩ፡ የሚከተለው ነው።

በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው ጸንተው፡ ቅን የኾነውን የታማኝነት አገልግሎታቸውን፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በማበርከት ላይ የሚገኙት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ካህናት፡ በዓለሙ የኀዋ አውታሮች በኩል የሚሠራጩትንና የሚተላለፉትን መልእክቶች ስለሚከታተሉ፡ በእርስዎና እርስዎን በመሰሉት፡ የፀረ ኢትዮጵያ ኃይላት ጎራ በኩል እየተነዛ ያለውን ሓሣዊ መልእክት፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ደረሱበት፤ ያም፡ እናንተ፡ ለቴዎድሮስነት ያጫችሁትና ያዘጋጃችሁት፥ እርሱም፡ ራሱን ያጨና ለዚሁ ያዘጋጀ፡ አንድ ሰው መኖሩን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

በዚህ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእርሱ ገላጪነት፡ እነርሱ የተረዱትን፡ ያን፡ የእርስዎንና የመሰሎችዎን ሓሳዊ ተልእኮ፡ በእግዚአብሔርዋ እውነት ለማጋለጥ እንዲችሉ አደረገ። ይኸውም፡ ባገር ውስጥም ኾነ በውጭ አገር፡ ቀደም ብለው፡ ወደእኔ፡ እየመጡና በመገናኛ መስመሮች እየቀረቡኝ፡ በድፍረት፡ *"እኔ ቴዎድሮስ ነኝና፡ እውቅናን ሰጥተህ ታዘዘኝ!"* ላሉኝ ኹሉ፡ የሰጠሁት የጽሑፍ መልስ፡ ወደሚገኝበት ቤተ መዛግብት፡ እንደማናቸውም ጊዜ፡ አኹንም፡ መንፈስ ቅዱስ መርቶ ወስዶ፡ እርስዎ፡ የተጻፈበትን ቀን ሳይቀር የጠቀሱትን፡ ያን፡ እርስዎና መሰሎችዎ የተጋለጣችሁበትን፥ የተደናገጣችሁበትንና እጅግ የቆሰላችሁበትን፥ እኔም፡ ወዲያው፡ ከኹለት ቀናት በኋላ፡ መልስ የሰጠሁበትን ደብዳቤ፡ እዚያ አግኝተው፡ ይፋ ሊያወጡት መቻላቸው ነው።

እርስዎ ግን፡ በእኔ የመልስ ደብዳቤ ዓናት ላይ፡ "ኅዳር ፲፮ ቀን፥ ፲፱፻፺፭ ዓ. ም." ተብለው፡ በጉልህ የተጻፉትን ቃላትና አኀዛት ማየት እንዴት እንደተሳነዎ ለመረዳት ያዳግታል።

፪ኛ. *"ሌላው አብይ ጉዳይ ግልባጭ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የሚለው ነው፤ ፍየል ወዲያ ቅምዝምዝ ወዲህ እንዲሉ አበው፡ የሆነው ይኸው ነው።"* ላሉት፡ መልሴ አጭር ነው።

በቅድሚያ ግን፡ እርስዎ፡ ለዚህ ጉዳይ፡ የአበውን አነጋገር እንደተጠቀሙ ኹሉ፡ እኔም፡ በእነርሱው አነጋገር በመጠቀም፡ ስለዚሁ፡ ስላነሡት ዝክረ ነገር የምጠቅስልዎ፡ "የዐይጥ ምስክሩዋ ድንቢጥ!" የሚለውን ይኾናል። ኹላችሁም፡ አንድ ዓይነት የእምነትና የተግባር አቋም ያላችሁ ናችሁና። በዚህ ረገድ፡ የኹላችንም ፈጣሪና ባለቤት የኾነው፡ እውነተኛው ፈራጅና ባለዋጋ ስላለ፡ በኹሉ ላይ ለሚፈርድና ለኹሉ ተገቢ ዋጋን ለሚከፍል፡ ለእርሱ፡ ኹሉንም እንተወው።

በጠቀሱት ደብዳቤ ላይ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ ግልባጭ እንዲደርሳቸው ያደረግሁት፡ "ቴዎድሮስ ነኝ!" ባዩ ሰው፡ ያን ደብዳቤ፡ በዋና ባለአድራሻነት የጻፈው፡ ለእርሳቸው፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ በመኾኑ ነው። ሰውዬው፡ ለእኔ የጻፈልኝ፡ በግልባጭ እንጂ፡ በዋናነት እንዳልነበረ፡ እውነታውን አውቀው፡ ስሜታዊ አስተሳሰብዎን እንዲያስተካክሉ አሳስብዎታለሁ።

፫ኛ፡ *"ንጉሥ ቴዎድሮስ ዘኢትዮ... ለሚለው ጽሁፍ የሰጡት ምላሽ ልብ የሚሰብር እውነትን አጉልቶ ያላሳየ የተድበሰበሰ ነው"* ላሉት፡ አዎን! ልክ ነዎት። በመለኮታዊው የትስብእት ቃል፡ "የሓሰት አባት!" የተባለው የዲያብሎስ ጭፍሮች ለኾናችሁት፡ ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉት ሓሳውያን (አሳሳቾች)፡ *"ንጉሥ ቴዎድሮስ ዘኢትዮ... ለሚለው ጽሁፍ የሰጡት ምላሽ"* በእርግጥ፡ ልባችሁን የሚሰብር ነው፤ የመልስ ደብዳቤዬ፡ መንፈስ ቅዱሳዊና እሳታዊ ተልእኮም፡ አዎን! የሓሳውያንን ልብ፡ እንዲህ መስበር ነው፤ እነሆ፡ በእርስዎ ላይ ደርሶ እንደሚታየው፡ ተልእኮውን ፈጽሟል ማለት ነው፤ እርስዎን በመሰሉትም ላይ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ፡ እየፈጸመው እንደኮነ አምናለሁ።

እውነት፡ እርሷም፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ አንዲት ናት፤ ከፀሓይ ብርሃን ይልቅ፡ ጐልታ ትታያለች እንጂ፡ አትድበሰበስም። እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ "እውነት" የምትሉት ግን፡ የዲያብሎስን ሓሰት መኾኑ፡ ከፍሬአችሁ ታውቋል።

ለመኾኑ፡ ያች የእግዚአብሔር እውነት፡ ሕያዋንና አማናውያን መገለጫዎቿ ከኾኑት፡ አምላክን ከወለደችው፡ ከኢትዮጵያዋ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከአንዱ፡ ከኢትዮጵያዊው ልጇ፡ ከመሢሑ ኢየሱስ በላይ፡ እንዴት ኾና ተከሥታና ጐልታ እንድትታይ ነው የምትፈልጉት? እናንተ፡ ይኼን ግዙፍ እውነታ ማየት ተስኗችሁ፡ በዕውርነት የምትኖሩ፥ በዚህም፡ ዕውርነታችሁ፡ ሌሎች፡ የሚያዩትን ሳይቀር፡ እያሳወራችሁ፡ ድቅድቅ ጨለማ ወዳለበት ገደል የምትወረውሩ አይደላችሁምን? አዎን፡ መኾናችሁንማ፡ እነሆ፡ በመራራው ፍሬአችሁ፥ ይኸውም፡ በእየራሳችሁና በሕዝቡ ላይ በምትፈጽሙት፡ በክፋትና በጥፋት ሥራችሁ፡ እያረጋገጣችሁ መኾኑን፡ ፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ እየተመለከተው ነው።

ያ፡ "ይመጣል!" የምትሉት "ቴዎድሮስ"፡ መጥቶ፡ ዛሬ በመከከላችሁ እንዳለስ፡ ለይታችሁ የምታውቁት፡ እንዴት ነው? ሊያሳምናችሁ የሚችለው ምልክታችሁ ምንድር ነው? "ነስሑ! እስመ ቀርበት መንግሥተ እግዚአብሔር!" ማለትም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና፡ ንስሓ ግቡ!" እያለ በምድረ በዳ ሲጮህ፣ በዮርዳኖስም ሲያጠምቅ የነበረው ዮሓንስ መጥምቅ፡ በኤልያስ መንፈስ

የመጣው፡ "ኤልያስ" መኾኑን፥ እንዲሁም፡ "ነስሑ! ወተቀበልዋ ለመንግሥተ እግዚአብሔር! እንተ ሀለወት እማእከሌክሙ!" ማለትም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በውስጣችሁ ናትና፡ በንስሓ ተቀበሏት!" እያለ፡ በመካከላቸው ይመላለስ የነበረውን፡ "መሢሕ ኢየሱስን"፡ አይሁድ፡ አይተዋቸውና አውቀዋቸው፡ ሊቀበሏቸውና ሊያምኑባቸው እንዳልቻሉ ኹሉ፡ እናንተም፡ ዛሬ፤ ያ፡ "ይመጣል!" የምትሉት "ቴዎድሮስ"፡ መጥቶ፡ በመካከላችሁ እያለ፡ ልታውቁትና ልትቀበሉት፡ ምናልባት አልቻላችሁ እንደኾነስ፡ ይህን እውነታ አስተውላችሁታልን? አይመስለኝም። (ማቴ. ፫፥ ፪፤ ፬፥ ፲፯፤ ፲፩፥ ፲፩-፲፭፤ ፲፯፡ ፲፩-፲፫። ሉቃ. ፲፯፥ ፳-፳፩።)

በድንግል ማርያምና በልጇ፡ በመሢሕ ኢየሱስ ሕያዋን ሰውነት ተገልጣ፥ ገዝፋና ጐልታ የታየችው፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ ዛሬ፡ በመንፈስ ቅዱስ እየተናገረችን ያለችውእኮ፡ እናንተ "ቴዎድሮስ" የምትሉት እርሱ፡ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይኾን፡ ፍጥረተ ዓለሙን፡ አንድ አድርጎ የሚመራውና የሚያስተዳድረው፡ የዓለሙ ንጉሥ፡ በመካከላችን ያለ መኾኑን ነው። እርሱም፡ ኢትዮጵያዊው መሢሕ ኢየሱስ ነው። ንግሥቲቱም፡ ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም ናት። እርሱ፡ በሊቀ ካህናትነትና በንጉሠ ነገሥትነት፥ እርሷ፡ በእናት አገርነትና በንግሥተ ንግሥታትነት የሰፈኑባት ዘውዳዊ ዘፋናቸውም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት። የዚች መንግሥት፡ ሕዝቦቿና ግዛቷም፡ በሰማይና በምድር የሚኖሩት ፍጡራኑና ፍጥረተ ዓለማቱ ናቸው።

ባለፈው፡ በ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት፡ በጎዋ የነጋሪት ድምፅና ሰሌዳ ላይ፡ በይፋ የተደመጠውና ተጽፎ የተነበበው፡ የአዋጅ ቃል፡ ታዲያ! ምን መስሎዎት ኖርዋል? ይኼ እውነታ አይደለምን? ነው እኮ! አዬ! አለማመን፡ እንዴት ክፉና ጠንቀኛ ችግር ነው!

ይህ፡ የእናንተ "ቴዎድሮስ"፡ በእግዚአብሔር ወልድነቱ፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረት በፊት፡ ከእግዚአብሔር አብ፥ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ከድንግል ማርያም፡ በትስብእትነት ከተወለደው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ይበልጣልን? ከእርሱ፡ ከኢትዮጵያዊው መሢሕ ኢየሱስ በቀር፡ ሌላ ቴዎድሮስን የምትፈልጉና የምትጠብቁ ከኾነ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዲህ ሲል የተናገረው ቃል የሚጸናባችሁ ይኾናል፡-

"ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።"

ማለትም፡ "ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።"

ይህ መለኮታዊ የትስብእት ቃል የተነገረው፡ ለዐንገተ-ደንዳናዎቹ ተቃዋሚዎቹ፡ ለአይሁድ እንጂ፡ ለታመኑት የቅዱሱ ኪዳን ወገኖቹ፡ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ስላልኾነ፡ የእርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ የማን ወገኖች እንደኾናችሁ፡ ይኸው፡ በዚህ፡ በዓመፅና በክህደት ሥራችሁ

እየመሰከራችሁ ነው። "ቴዎድሮስ" ከምትሉት፡ የሚበልጠውን፡ እርሱን፡ ኢትዮጵያዊዉን መሢሕ ኢየሱስን፡ እስከዛሬ፥ ዛሬና ወደፊትም፡ በዚህ ማንነቱና ምንነቱ እንኳ፡ ልትቀበሉት አልቻላችሁምና። (ማቴ. ፲፪፥ ፴፪።)

ይህ ብቻ አይደለም፤ እጅግ የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው፥ የሚያሳፍረውና የሚያሳዝነውም፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ በምንኵስና ቀንበር ተጠምዳችሁ የምትገኙ ወገኖች፡ "ኢትዮጵያውያን ነን!" እያላችሁ፡ ከእግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች ኹሉ የተሰጠውን፥ ነገር ግን፡ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፡ ከሌሎቹ የዓለም ሕዝቦች ተለይተው፥ ተቀብለውትና አጽንተውት የኖሩበትን፡ ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ በትክክል አለማውቃችሁ ነው።

አዎን! ከኪዳነ አዳምና ከኪዳነ ኖኅ ቀጥሎ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሦስተኛ አካል በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ኪዳን ምክንያት፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ፡ በመሠረቱና በቀላሉ ልታውቁትና ልትቀበሉት፥ ልታምኑበትና ልትኖሩበት የሚገባችሁን፡ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ሕይወት እንኳ ያልተረዳችሁ መኾናችሁ ነው። ታዲያ! ራሳችሁ ካላወቃችሁት፡ እንዴት፡ ለሌላው ላላወቀው ልታሳውቁ ትችላላችሁ? አትችሉም።

ይኸውም፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወንድ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት ሴት፡ እየራሳቸው፡ እናንተ የምትሉት "ቴዎድሮስ" መኾናቸው ነው። አዎን! በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ገና ከአባታቸው አብራክና ከእናታቸው ማሕፀን ጀምረው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፥ ነጋሾች (አጼ/አጼዪት) እና ካህናት (አገልጋዮች) ኾነው፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ተወልደዋል፤ ተገርዘዋል፤ ተጠምቀዋል፤ ተቀብተዋል።

ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ደርሰው፡ ይህን ምንነታቸውንና ማንነታቸውን፡ በሃይማኖት እውቀትና በምግባር ፍሬ ሲያጸኑት፡ ለዚያ መለኮታዊ ጸጋና ክብር፥ ማዕርግና ሥርዓት፡ የበቁ ኾነው የኖሩበትን የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት ይሠሩበታል፤ ያገለግሉበታል፤ ይሠየሙበታል።

ታዲያ! ይኼ ዘለዓለማዊ መለኮታዊ በረከት፡ እንኳንስ መሢሕ ኢየሱስን፡ እያንዳንዱን ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷን ኪዳናዊት ኢትዮጵያዊት፡ ለዚያ "ቴዎድሮስነት" የሚያበቃ አይመስልዎትምን? ቢመስልዎ ይሻላል። ለዚህ እኮ ነው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ልጆች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ የአገልግሎት ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ውስጥ የሚሠየሙትን አባሎች፥ ምሉኮችና ካህናት፥ አጼውን፥ ወይም፡ አጼዪቱን ሳይቀር፡ ለመምረጥም ኾነ፡ እየራሳቸው ለመመረጥ፡ ምንም ዓይነት ችግርና ውዝግብ የሌለባቸው።

በመሢሕ ኢየሱስ ያየነውና ያውቅነው፡ የሰማያዊው አባታችን፡ የልዑል እግዚአብሔር እና በድንግል ማርያም፡ ያየናትና ያወቅናት፡ የዘለዓለለማዊቷ እናታችን፡ የኢትዮጵያ ፈቃድና ደስታ፥ ያደረጉልንም ቸርነት፡ እኛ ሰዎች፥ ወንዶችም፥

ሴቶችም፡ እያንዳንዳችን፡ እየራሳችንን፡ ለዚህ "ቴዎድሮስነት" እንድናበቃ እንጂ፡ በየጊዜው፡ "ቴዎድሮስ ይነሣል! ይመጣል! ነጻ ያወጣናል! ፍቅርንና ሰላምን ያሰፍንልናል! ብልጽግናን፡ እንደመና ያወርድልናል! ተድላ ደስታን ያጎናጽፈናል! የፀጥታ ዕረፍትን ያቀዳጀናል!" እያልን፡ በስንፍናና በምኞት ተተብትበን፡ ስንቆዝምና ስንሠቃይ እንድንኖር አይደለም።

እናንት፡ እየራሳችሁን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" እያላችሁ፥ ነገር ግን፡ አለመኾናችሁን፡ በምትገኙበት የጕሥቍልና ኑሮ ዓይነት የምታረጋግጡ ሰዎች ኹሉ! በዚህ፡ ክፉ ልማድ ተመርዛችሁ፡ በመጨረሻ፡ ደም እስከማፍሰስ በደረሰ ጭካኔ፡ እርስ በርሳችሁ ስትተላለቁ ያሳለፉችኋቸው፡ በሺሆች ዓመታት የሚቆጠሩት ዘመናት፡ እንግዴህ አይበቋችሁም? ዛሬ ያላችሁበትስ፡ የእርስ በርስ እልቂት፡ ይኸው፡ በበለጠ ረቂቅነትና ጥልቀት፥ ስፋትና ምጥቀት እንደቀጠለ አይደለምን? ይህ አሠቃቂ የዲያብሎስና የጭፍሮቹ ክፉዎች ሰዎች ግፍና በደል፡ እስከመቼ ነው እንዲካኼድ የምትፈልጉትና የምትደግፉት? የምትስማሙበትና የምትተባበሩበት? አይበቃችሁም? ጽዋው ሞልቶ እየፈሰሰ መኾኑን አትመለከቱም?

ርኩሱ መንፈስ ከሚያደርገው በላይ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹላችሁ፡ የእርሱ ግብረ አበሮች ኾናችሁ፡ *"ወደፊት የምትነግሠው፡ መጪው ቴዎድሮስ አንተ ነህ!"* እያላችሁ፡ እስከዛሬ፡ በምሥጢርና በሥውር፥ በጨለማና በተንኰል፡ ሕዝቡን፡ እርስ በርሱ እያጋጫችሁ ስታስተላልቁትና ስትፈጽሙበት የኖራችሁበትን ሰይጣናዊው ግብራችሁን፡ ዛሬም፡ ያንኑ ለመቀጠል፡ ታጥቃችሁ በመነሣት፡ በሰላም እየሠራ ሊኖር የሚገባውን ደካማ ሰው እየፈለጋችሁ፡ ራሱንና ቤተሰቡን፡ ለታላቅ የሕይወት አደጋ፥ ለእሥራትና ለሞት ጭምር መዳረጋችሁ፥ ኅብረተ ሰቡንም፡ በዚህ የተሳሳተ እምነት በክላችሁ ማመሳችሁ፡ አዎን! እጅግ ያሳዝናል። በዚህ ክፉ ሥራችሁ፡ አኹን፡ በሕይወተ ሥጋ፡ በምድር ላይ፥ ኋላም፡ በሕይወተ ነፍስ፡ በሰማይ፡ በልዑሉ ፈጣሪና በቅድስት እናቱ የፍርድ ዙፉን ፊት እንደሚያስጠይቃችሁ አታምኑምን? ብታምኑና ብታጤኑት ይበጃችኋል።

ከዚህ ኹሉ ሓተታ የተነሣ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእርሱ፡ ከመሢሕ ኢየሱስ በቀር፡ ሌላ የምትጠብቀው፡ "ቴዎድሮስ" የለም። እነመልከ ጼዴቅ፥ እነዮቶር፥ እነንግሥት ማክዳ፥ እነቅዱስ ላሊበላና እነቀዳማዊ ቴዎድሮስ፡ አርአያዎቹና ምሳሌዎቹ የኾኑት፡ ስመ ጥሩው፡ የእናንተ "ቴዎድሮስ" ቢያስፈልገን እንኳ፡ ለእኛ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ልጆች፡ ኢትዮጵያዊው ወገናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይበቃናል።

ኹላችን፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን በቅተንና በንስሓ እየራሳችንን አስተካክለን በምንገኝበት ጊዜ ደግሞ፡ በመለኮታዊው ሥርዓታችን መሠረት፡ እርሱና ቅድስት እናቱ፡ በእኛው መራጭነትና ተመራጭነት፡ ከመካከላችን ሠይመው በሚሰጡን "ቴዎድሮሳዊ"፥ ወይም፡ "ቴዎድሮሳዊት" አገልጋይ እንገለገላለን።

እናንተ ግን፡ ራሳቸውን፡ "ራስ ተፈሪዎች" ብለው የሚጠሩት ወገኖች፡ ኢትዮጵያዊዉን መሢሕ ኢየሱስን ትተው፡ በእርሱ ቦታ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን

እንዳስቀመጡ ኹሉ፡ እናንተ ደግሞ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፡ ሌላ "ቴዎድሮስ"ን ከፈለጋችሁ፡ የእነርሱ ብጤዎች መኾናችሁ ነውና፡ ስለዚሁ ስሕተታችሁ፡ በብርቱ አስባችሁበት፥ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮም ኾናችሁ፡ ጸልያችሁበት፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደእውነተኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ እንድትመለሱ፥ በእርሱም እንድትጸኑ፡ ከተለመደውና ከማይቋረጠው ጸሎታችን ጋር አሳስባችኋለሁ።